*“የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሳጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።”*

*2ኛ ጢሞ 3፡16-17*




ቦስተን የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን የሥነ-ጽሑፍ አገልግሎት
በሁለት ወር አንድ ጊዜ እየተዘጋጀ የሚቀርብ መንፈሳዊ ጋዜጣ

# በውስጥ ገጾች

❖ **<u>ዕርሰ አንቀጽ፤</u>**

- **ተናገር ዝም አትበል፤**

 የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር የተላከውን ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ባለማመን የሃጢያት እዳ የሆነው ሞት በእርሱ ላይ ነግሶበት ይኖራል።

❖ **<u>እንግዳችን፤</u>**

- ከእንቅልፌ ልነሳ አካባቢ እግዚአብሔር ይፈልግሃል የሚል ድምጽ ወደእኔ በተደጋጋሚ ሲመጣ እየሰማሁ እኔም እግዚአብሔር እኔን አይፈልገኝም እያልኩ ከራሴ ጋር በመሟገት ላይ እያለሁ ከእንቅልፌ ነቃሁ።

❖ **<u>የተመጣጠነ ምግብ፤</u>**

- ወደ እውነቱ ስንመጣ ለሰውነታችን ለጤናችን እና ለሥጋችን ተጠንቅቀን እንደምንመገበው ያውም አሁን በልተን ለሚጠፉ ይህን ያህል ስናማርጥ እና ስንጠነቀቅ ለመንፈሳችን ግማሹን ያህል እንኳን ተጠንቅቀን ከቃሉ ማእድ መግበነው ይሆን ?

❖ **<u>የእውነተኛ ክርስቲያን ባህሪ፤</u>**

- እንግዲህ የእግዚአብሔር ቃል የሚያመለክተን በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ዳግመኛ በመወለድ የእግዚአብሔር ልጆች የሆንን የእ/ግ ሕዝብ መለያችን ቃሉን በማመን መታዘዝ ነው።

በቦስተን የምትገኘው የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ የምታምን የክርስቶስ ኢየሱስን የማዳን ወንጌል ባገኘችው አጋጣሚ ሁሉ የምታሰራጭ ቤ/ክ ነች። ይህም ጋዜጣ ወንጌልን ከምታሰራጭባቸው መንገዶች አንዱ ሲሆን በቤ/ክ የሥነ-ጽሁፍ አገልግሎት አባላት እየተዘጋጀ በየሁለት ወር አንድ ጊዜ ይቀርባል።

**የቤተክርስቲያኒቱ መጋቢ**
**ፓስተር ምሕረቱ ሌጂቦ**
Email Meheretu2614@Yahoo.com
Telephone 617-792-5764

ዋና አዘጋጅ...................... ሄኖክ ተሾመ
ምክትል አዘጋጅ ..............ሐብታሙ አስረስ
የውብዳር ፍስሐ
ኮምፒዩተር ዝግጅት ........ትርሲት ጥላሁን
የፊት ገጽ ዲዛይነር.............ዘነበ ምትኩ

ለቀጣዩ እትም ይረዳ ዘንድ የእናንተ ተሳትፎ ወሳኝ ሚና ስላለው በሚቀጥለው አድራሻ ያላችሁን አስተያየትና ጥያቄ ላኩልን።

አድራሻ:
Ethiopian Evangelical Church in Boston
88 Tremont Street
Boston, MA 02108
Tel. 617-816-8827
E-mail: Henokekka@yahoo.com



የእግዚአብሔር አምላካችን ቃል ሕያው ነው አይለወጥም!

## ርዕሰ አንቀጽ፤

## ተናገር ዝምም አትበል፤

እግዚአብሔር ለዓለም ሕዝብ ሁሉ መልእክት አለው ይህም መልእክት ሰዎች ሁሉ በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ በማመመን ከዘለአለም ሞት እንዲያመልጡ እና ሰዎች ሁሉ ሊመለክ የሚገባውን እግዚአብሔርን ያመልኩ ዘንድ እርሱን በማወቅና በማመን የሚገኘውን ሕይወትና እረፍት እንዲያገኙ ነው።

እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን በመላክ የሰው ልጅ ሁሉ ከእርሱ ጋር የሚገናኝበትን መንገድ ዘርግቷል፤ የሰው ልጅ ከአብ ዘንድ የተላከውን ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ባለማመኑ የኃጢአት እዳ የሆነ ሞት በእርሱ ላይ ነግሶበት ይኖራል፤ ከዚህ የተነሳ ለጨለማው ስልጣን ተገዢ ሆኖ የዲያብሎስን ፈቃድ በማድረግ ሳይወድ የግዱን ሊያደርግ ያልፈለገውን የክፉን ፈቃድ በማድረግ እርካታና እረፍት ሳያገኝ ሰቆቃ የበዛበትን መራራ ሕይወት በመኖር ይቅበዘበዛል። የምድር ስቃይና መከራ አላፊ ቢሆንም ሰው በክርቶስ ኢየሱስ ባለማመኑ መከራውና ስቃዩ በምድር ብቻ አያበቃም በክፋና በጠነከረ መልኩ መ ጨረሻ የሌለው የዘለአለም ፍርድና ስቃይ ከፊቱ ይጠብቀዋል፤ ይህም ስቃይ ለዲያብሎስና ለጭፍሮቹ ለዘለዓለም እንዲኖሩበት የተዘጋጀላቸው የእሳት ባህር ነው።

ለዘለአለም በእሳት ባህር ውስጥ መኖር እንዴት አሳዛኝ ነው፤ ከዚህ ፍርድ በበጉ ደም በመንጻት ከጨለማው ስልጣን መንግስት አምልጠን ወደፍቅሩ መንግሥት የፈለስን እኛ በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ጣፋጩን ህይወት ያገኘን ይህን የምሥራች ይዘን እንዴት ዝም እንላለን የያዝነውን መድኃኒት ለሰዎች እናውጅ፤ ከዘለዓለም ፍርድ ያምልጡ ከሲኦል ይዳኑ ከዲያብሎስ እጅ ነጻ ይውጡ እንናገር ዝምም አንበል።

የቤተክርስቲያኒቷ መልዕክት



## <u>እንግዳችን</u>

ካለፈው የቀጠለ... ወንድም ለቤዛ ዓለሙ ከነበሩበት አሳዛኝ የሕይወት ውጥንቅጥ የተነሳ እራሳቸውን በመድሃኒት ለማጥፋት ወስነው ወደ አንድ ሆቴል በመሄድ መኝታ ክፍል ተከራይተው መድኃኒቱን ለመውሰድ ድፍረት እንዲያገኙ መጠጥ ጠጥተው ወደ ክፍላቸው እየሄዱ..ቀጣዩን እነሆ፤

ክፍሉ ውስጥ እንደገባሁ ከስካርና ከድካም የተነሳ ይመስለኛል እንዴት እንደረሳሁት ባላውቅም በሩን መለስ አድርጌ ከእነልብሴ አልጋው ላይ በጀርባዬ ተንጋልዬ ተኝቻለው ብዙም ሳልቆይ ያለሁበት ክፍል በር በኃይል ተበርግዶ ሲከፈት ደንግጬ ብድግ አልኩ ሁለት ጓደኞቼን ፊት ለፊቴቆመው አየኋቸው በጊዜው እንዴት እንደመጡ ማን እንደነገራቸው ባላውቅም በኋላ ሲነግሩኝ ግን የሆቴሉ ሥራ አስኪያጅ እንደደወለላቸው ነግረውኛል፤ እንደ ቆምኩ ከአልጋው አጠገብ ወዳለው ኮሞዲኖ ላይ ያስቀመጥኩት መርዝና ውኃ ቁጭ ብሏል ቀስ ብዬ እጄን ዘርግቼ መድሃኒቱን አንስቼ በኪሴ ከተትኩት እነርሱም ምን እንደሆነ ስላለወቁ አልጠየቁኝም ወዲያውኑ ወደ ቤት እንድንሄድ ጠየቁኝ እንደማይተውኝ ስላወቅሁ ከእነርሱ ጋር ወደ ቤቴ ሄድኩ ቤት ስንደርስ ሰዓቱ በጣም መሽቶ ነበር ባለቤቴ ደንግጣ ምን እንደተፈጠረ ግራ ገብቷት ተቀበለችኝ ጓደኞቼም አድርሰውኝ ሄዱ እኔም ከባድ ድካም ስለነበረኝ ተኛሁ፤ ከእንቅልፌ ልነሳ አካባቢ እግዚአብሔር ይፈልግሃል የሚል ድምጽ ወደ እኔ በተደጋጋሚ ሲመጣ እየሰማሁ እኔም እግዚአብሔር እኔን አይፈልገኝም እያልኩ ከራሴ ጋር በመሟገት መሃል እያለው ከእንቅልፌ ነቃሁ ወዲያውኑ ባለቤቴን ከዚህ በፊት አንድም ቀን ጠይቄአት የማላውቀውን ይዛኝ ወደ ቤተክርስቲያን እንድትሄድ ጠየቅኋት እርሷም በደስታ ጥያቄዬን ተቀብላ ይዛኝ ሄደች ስንሄድ ያገኘነው ወንጌላዊ ታደሰ አወቀ ይባላል አሁንም በጎተራ ሙሉ ወንጌል በፓስተርነት ያገለግላል፤ ለእርሱም ያሳለፍኩትን ነገር ሁሉ ሳልደብቅ ነገርኩት ራሴን ለማጥፋት ያዘጋጀሁትንም መርዝ ከኪሴ አውጥቼ ሰጠሁት፤ በህልሜ ያየሁትንም ነገርኩት በጣም ለረጅም ሰዓት አጠገቤ ተንበርክኮ ጸለየልኝ እርሱ እየጸለየልኝ በውስጤ ልዩ የሆነ ስሜት ያልፍ ነበር ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግን የሆነው ነገር ትዝ አይለኝም ስነቃ ልዩ የሆነ ደስታ ተሰማኝ መዳኔን በሰውነቴ አወቅሁት አዲስ ሰው እንደሆንኩ ሰውነቴ ሁሉ ቀለለኝ የደስታ ልቅሶዬን ለማቋረጥ አልቻልኩም ድኘ ቀረሁ። የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን ያ ያሰቃየኝ የነበረ የመጠጥ ሱስ በራስ አለመተማመን ሁሉ ከውስጤ ተነቅሎ ወጣ በምትኩ ሰላምና ደስታ በውስጤ ፈሰሰ ጓደኞቼ የሚያውቁኝ ሁሉ በእኔ ላይ ስለታየው ለውጥ ለማመን ለብዙ ጊዜ ተቸግረው ነበር እንዲያውም ተመልሶ ይመጣል ብለው ይጠባበቁ ነበር ቤተሰቦቼና ወንድሞቼ እህቶቼም እንደዚሁ ነገር ግን እንደሱ አልሆንም እነሱን ያ እኔን የነካው ፍቅሩ ነክቶአቸው እነሱ እኔ ወዳለሁበት የእረፍት የሰላም ዓለም መጡ የእኔ መዳን እስከ ዛሬ ድረስ ይገርመኛል የእግዚአብሔርን ታላቅ ኃይል ሁሉን ቻይነት ከሞት ማስመለጥ እንደሚችል በህይወቴ ስላየሁ ዘወትር ይደንቀኛል ይገርማኛልም የነበርኩበትን አሁንም ጓደኞቼ የማውቃቸው ዘመዶቼ ሌሎችም ጌታን የማያውቁ የሚያልፍበትን ህይወት ሳስብ በጣም አዝናለሁ እኔ ጌታ ደርሶልኝ ድኘ ታሪኬን ተናገርሁ ይህ የእኔ ታሪክ ግን የብዙዎቹ ጌታን እንደግል አዳኛቸው ያልተቀበሉ ታሪክ ነው እንደ እኔ መርዝ ጠጥተው እራሳቸውን ለማጥፋት ባይሞክሩም በመጠጡ ብዛት በሽታው ስንቶቹን ጓደኞቼን ፈጅቷል፤ እየፈጀም ነው። በዓለም ስንኖር ሰይጣን የዘረጋው ብዙ ዘርፍ ያለው ችግሮች በህይወታችን ይገጥሙናል ሰላም የሚነሱ ብዙ ነገሮች በየቀኑ አሉ ከእነዚህ ወጥመዶች በራስ ማምለጥ አይቻልም ሰዎች ይሞክራሉ እኔም ብዙ ሞክሬአለሁ ግን አልቻልኩም ስለዚህ መፍትሄው ሸክማችንን ሊሸከም በደጅ የቆመውን እየሱስን እንደግል አዳኝ አድርጎ መቀበል ነው። የቤተሰቤን ሕይወት ጌታን እንደ ግል አዳኜ አድርጌ ከመቀበሌ በፊት ምን ትርጉም እንዳለው ለማስታወስም ለማስረዳትም አልችልም፤ ነገር ግን ትርጉም የሌለው ሕይወት እንደነበረ አውቃለሁ፤ ከባለቤቴና ከልጆቼ ጋር ብዙ ጊዜ ከሌለኝ የቤተሰቤን ፍቅር ለማወቅ ለእኔም ለእነሱም አስቸጋሪ ነበር ደግነቱ እኔን ባይተኩም ባለቤቴም ልጆቼም ባይተዋርነት እንዳይሰማቸው ብዙ ዘመዶች በዙሪያቸው ስለነበሩ ደህና ነበር በመሠረቱ በመጀመሪያም የትዳርንና የቤተሰብን ምንነት በትክክል ሳልረዳ ስለሆነ ትዳርን የመሠረትኩት ለዚህ ተቋም መደረግ የሚገባውን እንክብካቤ ኃላፊነቴን አላውቅም ነበር የሚያስፈልጋቸውን ነገር ገንዘብ ስላለ ማድረግ ከቻሉና እኔ ደግሞ ያንን ማቅረብ ከቻልኩ ግዴታዬ እዚህ ድረስም ይመስለኝ ነበር ብዙዎቹም በግዜው በቤቴ ውስጥ የሚደገሰውን ድግሥ የሚጠጣውን የሚበላውን እያየ እንደ እርሱ ቤቱን የሚመራ የለም ይሉ ነበር እኔም ይህንን ለእኔ ማድረግ ቀላል ስለነበረ አዘወትረው ነበር፤ ትክክለኛ ነገር ለቤተሰቤ እያደረግሁ ነው ብዬም አምን ነበር ባለቤቴም ልጆቼም ለሥጋቸው የሚያስፈልጋቸው ነገር ስለማይጎድልባቸው በጥሩ ሁኔታ ላይ መሆናቸው ለብሰው ተጋጊጠው መውጣታቸው ሁሉ እንደእርሱ ቤተሰቡን የሚይዝ ሚስቱን የሚወድም ይባል ነበር፤ ነገር ግን ባለቤቴ በምን ውስጥ እንደምታልፍ እርሷ ታውቅ ነበር። ባለቤቴን ልጆቼን እንደማላውቃቸው ያወቅሁት ጌታን ካገኘሁ በኋላ ነው። ልጆቼም አያውቁኝም እንደገና እንደ አዲስ ነው ህይወት በቤቴ ውስጥ የተጀመረው አደርግ የነበረው ሁሉ ከንቱ እንደነበር በመጀመሪያ እውነተኛው ፍቅር ለባላቤቴ ለልጆቼ ማሳየት እንደነበረብኝ ተረዳሁ ለቤተሰቤ ምንም እንዳላደረግሁ ራቁቴን እንዳለሁ ተሰማኝ፤ ባለቤቴ ብቻዋንልጆቿን እንከዚያ እድሜአቸው ለማሳደግ የከፈለችው ዋጋ እስከ ዛሬ ደረስ ሳስታውሰው ያሳዝነኛል።



እንግዳችን አቶ ለቤዛ ዓለሙና ቤተሰቦቻቸው

ከእግዚአብሔር ጋር ቤተሰባችንን መምራት ስንጀምር ልዩ የሆን ፍቅር በረከት በቤታችን ይፈስ ጀመር እኔም ይበልጥ ደስ እያለኝ ለባለቤቴም ለልጆቼም ጊዜ በመስጠት አብሮ በማምለክ ኑሮአችንን በአዲሱ ጎዳና ተያያዝነው በዚህ መካከል እያለን እኔ ወደ አሜሪካን ሀገር መጣሁ ቀጥሎም ባለቤቴና ልጆቼ መጡ ጌታም በሚያስፈልገን ሁሉ ባረከን እኛም እግዚአብሔርን እያመሰገንን እንኖራለን። ልጆቼም ከልጅነታቸው ጀምሮ ይማሩ የነበረው በመንፈሳዊ ትምህርት ቤት ስለነበረ የጌታ ነገር እየሰሙ ያደጉና መጀመሪያ ከእናታቸው ጋር በኋላም አብረን በነበርንበት አካባቢ ቤተክርስቲያን በመሄድ ጌታን ስናመልክ፤ ስናገለግል ስለነበር ይህንኑ እንዲያሳድጉ እኛም አብረን የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናት፤ በመጸለይ ቋሚ ኘሮግራም በማዘጋጀት በቅርብ የምንከታተላቸው ሲሆን በትምህርታቸውም እንዲጠነክሩ በማሰብ ጥሩ ትምህርት ቤት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን በማመቻቸት በነፍሳቸውም በሥጋቸውም የሚያስፈልጋቸውን እንዲያገኙ ከእግዚአብሔር ጋር የምንችለውን ሁሉ ጥረት እናደርጋለን። በእነርሱም ዋጋ ፍሬ በሁሉም መስክ እያየን ስለሆነ እግዚአብሔርን እያመሰገንን በዚሁ እንዲቀጥሉ ደግሞ በጸሎት በምክር ዘወትር ከጎናቸው እንሆናለን። ቤተሰባችን በዓመት ቢያንስ አንድ ጊዜ የራሳችንን የፀሎት ጊዜ በመውሰድ በመጸለይ ለዓመቱ ከጌታ ራእይ በመቀበል እግዚአብሔርን እንዲያደርግልን የምንፈልገውን ደግሞ እያንዳንዳችን በእርሱ ፊት በፀሎት እራሳችንን በማቅረብ እግዚአብሔር ስላደረገልን ነገር ለማመስገን በኛ በኩል በድካማችን ባላከናወነው ነገር ንሰሃ በመግባት ከስህተታችን በመማር ለሚቀጥለው ዓመትም እንደዚሁ በማድረግ ሁለንተናችንን ለእርሱ በመሥጠት ውጤት ያገኘንበት ልምምድ አለን። በቤት ውስጥ ለእለት ተእለት ኑሮአችን ሁላችንም በመረዳዳት ሥራ በመከፋፈል ኘሮግራም አውጥተን እንሰራለን በማንኛውም ልጆቻችን ማወቅ የሚገባቸውን ጉዳይ ላይ በግልጽ እንወያያለን ለሚጠይቁትም ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ እንሰጣለን። በአገልግሎታችንም አንዳችን አንዳችንን በመደገፍ እናገለግላለን። በኑሮአችን በጣም ደስተኞች ነን ጠላት ባለቤቴን ያለባል ልጆቼን ያለአባት ሊያስቀር ሞክሮ ነበር አልተሳካለትም ጌታ ለእኔና ለቤተሰቤ ስላደረገው ቸርነት ስሙ ለዘለአለም የተባረከ ይሁን።

ወንድም ለቤዛ ዓለሙ የሰጡንን የሕይወት ምስክርነት ከሰማን በኋላ ባለቤታቸው ወ/ሮ ስንዱ አሰፋን እንዲህ ስንል ጠየቅናቸው።

እውነት.. ወንድም ለቤዛ አለሙ የነበሩበት ሕይወት እጅግ አሳዛኝ እንደነበር ከምስክርነታቸው ሰምተናል መቼስ ለእርሶ ያ ጊዜ ከባድ የጨለማ ዘመን ነበር፤ ያንን ዘመን ዛሬ ላይ ቆመው ሲያስቡት ምን ይሰማዎታል? አያይዘው ቢመልሱልን እንደዚህስ የተባረከ ዘመን ይመጣል ብለው አስበው ያውቃሉ?

እህት ስንዱ አሰፋ በፍጹም አሉን በህልሜም በሁኔም እንዲህ የተባረከ ዘመን ይመጣል ብዬ አላሰብኩም ያንንም ዘመን ሳስበው ይገርመኛል ደንዝዤ ነበር ወይ እላለሁ እንዴት ችዬ አለፍኩት ሳስበው ማመን ያቅተኛል አንዳንዴም ሕልም ይመስለኛል ግን እግዚአብሔር ፀጋን አብዝቶልኝ እንደነበር አስባለሁ እኔ እና ቤቴ የነበርንበት ችግር እግዚአብሔር ብቻ ሊፈታው እንደሚችል አምን ነበር። የባለቤቴ እውቀት ሥልጣኑ ገንዘቡ መፍትሄ ሊሆነን አልቻለም እኔ በልጅነቴ ጌታን አውቅ ነበር እህቶቼ ደግሞ በጌታ ነበሩ ታዲያ ልቤ ወደ ጌታ አዘነበለ በአንድ ወቅት ከመኖሪያ ቤታችን ትንሽ ራቅ ብሎ ኮንፍራንስ ይካሄድ ነበር የሚገርው እኔ እቤት ቁጭ ብዬ ድምጽ እቤት ድረስ ይመጣ ነበር ታድያ ባለቤቴን ወደዚያ ኘሮግራም ልመሄድ እንደምፈልግ ነገርኩት የኔ ባለቤት ሆነሽ እንዴት አለኝ በጊዜው የኢሰፖ አባልና ባለሥልጣን ስለነበር ነው፤ በዚያ ምክንያት ቀረሁ ያም ሆኖ ጌታ በተአምራቱ ወደቤቴ ገባ ነገር ሁሉ ተለወጠ ጌታ ይመስገን ሲሉ ምስክርነታቸውን ሰጥተውናል።

በመጨረሻ ይህ ቤተሰብ መንፈሳዊ አባታችን ነው በክርስትና ህይወታችን እንድናድግ አድርገዋል ያሏቸውን ፓስተር ታደሰ አወቀን ኢትዮጵያ ስልክ ደውለን አነጋግረናቸው ነበር።

እውነት...ፓስተር ታደሰ እንደምን አደሩ?

ፓስተር ታደሰ.. እግዚአብሔር ይመስገን ማን ልበል?

እውነት.. ከቦስተን የኢ.ወ.ቤ.ክ የሥነ-ጽሑፍ አገልግሎት ነው?

ፓስተር ታደሰ..መልካም ምን ልታዘዝ ?

እውነት..ወንድም ለቤዛ ዓለሙን ያውቋቸዋል ?

ፓስተር ታደሰ... በደንብ ጠንቅቄ አውቀዋለው መንፈሳዊ ልጄ ነው ምን እሱ ብቻ ቤተሰቡ ሁሉ ልጆቼ ናቸው።

እውነት፤- ቀጥልን እስኪ ስለ እሳቸው የሚያውቁትን ይንገሩን፤

ፓስተር ታደሰ.. አስታውሳለሁ እለቱ ሰኞ ነው በቤተክርስቲያችን ደንብ ሰኞ ሰኞ ፓስተሮችና ወንጌላውያን የእረፍት ቀናችን ነው በዚያን እለት ግን ለምን ወደ ቢሮ እንደገባሁ አላስታውስም ገብቼ ነበር በኋላ ስንዱ እና ባለቤቷ ወንድም ለቤዛ ወደእኔ መጡ ለስንዱ መንፈሳዊ ምክሮችን በመስጠት በመጸለይ ከጎኗ እቆም ስለነበር ምንው ምን ተፈጠረ አልኳት። ምክንያቱም ወንድም ለቤዛን ሳየው

በጣም ያዘነና የተረበሸ ፊት ነበረው ሁኔታው እኔንም በጣም አሳዘነኝ በኋላ ጌታን መቀበል እንደሚፈልግና እንድንጸልይላት ስንዱ ነገረችኝ ያሳለፈውንም የመከራ ዘመን እያንዳንዱም ዘርዝሮ ነገረኝ ወድኃኒቱንም አውጥቶ ሰጠኝ በኋላ ተንበርክኮ ጸለይኩለት ጌታን ተቀበለ የዛን እለት አስታውሳለሁ እቤቴ መሄድ እፈራለሁ እዚሁ እናንተጋ እንደር አለኝ ምክንያቱም ያ ጭንቀትና ፍርሃት ተመልሶ ይመጣል ብሎ በመፍራት። ነገር ግን ነገርኩት ጌታ ነፃ አውጥቶሃል ከዚህ በኋላ አንተ የጌታ ነህ አትፍራ ጭንቀትህ ተመልሶ አይመጣም መክሬ በግድ እየፈራ ወደ ወደቤቱ ሄደ በማግስቱ ጠየቅሁት ሰላም ነኝ አለ በሶስተኛውም ቀን ጠየቅሁት አሁንም ሰላም ነኝ አለ ክብር ለጌታ ይሁን። ይህ ወንድም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በሕይወቱ እያደገ እየተለወጠ ሄደ በኋላም ወደ አሜሪካ መጣ በጣም ፈርቼ ነበር፤ ብዙዎቹ አሜሪካ ገብተው ተውጠው ቀርተዋል ከዚህ የተነሳ ይህ ሰው ምን ይገጥመው ይሆን ብዬ ሰግቼ ነበር ነገር ግን እግዚአብሔር ይመስገን በነገር ሁሉ እድገቱ አላቋረጠም ስለእርሱ ጌታን እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ ሲሉ ምስክርነታቸውን ሰጥተውናል።

በሁለት ተከታታይ እትም አስደናቂ የሕይወት ምስክርነታቸውን የሰጡንን ወንድም ለቤዛ ዓለሙ በቀጣዩ እትም የመጨረሻ የሆነውን ስለ አገልግሎታቸው እና በአግሎታቸው ወቅት ስለገጠማቸው አንዳንድ ጉዳዮች ምስክርነታቸውን ይሰጡናል።

## <u>የተመጣጠነ ምግብ</u>

በሐገር ቤት ሳለን ስለተመጣጠነ ምግብ በኑሮ በዘዴ ከማመር ውጭ የተማርነውን በተግባር ለማዋል ጥረት አድርገን የምናውቅ ስንቶች እንሆን? ዛሬ ዛሬማ ስለ ዳይት፤ ካሎሪ፤ ቫይታሚን፤ ኘሮቲን፤ መታቦሊዝም ወዘተ. እያልን ብዙ እናወራለን ግሮሠሪ ስናደርግ ስንት ፐርሰንት ፋት ኮሮስሮል እንዳለው አገላብጠን እናያለን። ከዚህም አልፈን ለሰዎች ምን መመገብ እንዳለባቸው እንመክራለን የበሬ ሥጋና ቺዝ ብዙ ቅባት ስላለው በእንጬትም አትንኩት እንቁላል ሥታዩማ ሽሹ እርሱን መብላት ኮለስትሮለ ከነነፍሱ የመብላት ያህል ነው በተለይ በተለይ ጃንክ ፉድ ሜክዶናልድ በርገርኪንግ ፒሣ ፍሬንች ፍራይስም ብዙ ዘይትና ካርቦሃይድሬት አለው ያወፍራል፤ ቅርጽ ያሣጣል እዚህ ሃገር ከወፈሩ መመለሻው ከባድ ነው መርጣችሁ ብሉ እንላለን። ወገኖቼ ለስጋችን ወይም ለአካላችን ቅርጽ ማሰብ መንከባከብ መርጦ መብላት መልካም ነው ግን አንዳንዶቻችን ከልክ በላይ ከማሰባችን የተነሳ ዳይት ላይ ነን እያልን፤ እራትም እየተውን የታመምንም ደግሞ የበለጠ ሰውነታችን ጨምሮ የተቸገርንም አንጠፉም ያልሮጥነው ሩጫ፤ ያልሄድነው የእግር መንገድ ያልገባንበት ጂም የማናደርገው የሰውነት እንቅስቃሴ የለም ምንም እንቅስቃሴ የማናደርግ ጥቂት ሰዎች እንኳን ብንኖር ቀንና ሌሊት አእምሮአችን ስለሥጋችንና ሠውነታችን በጭንቀት ማናወዙ ሃቅ ነው። ታዲያ ወገኖቼ ይሄ ሁሉ ለስጋችን ጤናና ለሠውነታችን ቅርጽ ማሰባችን መጨነቃችን አይገርምም?

ወደ እውነቱ ስንመጣ ለሰውነታችን ለጤናችንና ለስጋችን አንዴ ከፍራፍሬ፤ ከአትክልት ከጥራጥሬ ከአሣ ዶሮ እያልን ተጠንቅቀን እንደምንመገበው ሊያውም አሁን በልተነው ለሚጠፋና ደግሞ ለሚርበን ይህንን ያህል ስናማርጥና ስንጠነቀቅ ለመንፈሳችን ግማሹን ያህል እንኳን ተጠንቅቀን ከቃሉ መዓድ መግበነው ይሆን? እኔ አይመስለኝም **እንደውም አንዳንዴ ሳስበው መንፈሳችንን በጣም ከቃሉ መግበነው ስለወፈረብስን ለመቀነስ ዳይት ላይ ሆነን ይሆን አንዴ ከእግዚአብሔር ቃል ምግብ የማንመገበው ወይም ትንሽ ቀመስ ብቻ አድርገን ዘወር የምንል ልክ ለስጋችን ውፍረት መቀነስ ራት እንደማንበላ ሁሉ ለመነፈሳችንም እንዲሁ ?**

መቼ ነው ለሰውነታችን ለምንሠራው ምግብ የተለያዩ ዓይነት ቅመሞችን ገዝተን እንደምናጣፍጠው ሁሉ ለነፍሳችንና መንፈሳች ህይወት ማጣፈጫ ከዳዊት ከምሣሌ፤ ከዘፍጥረት፤ ከኤፌሶ፤ ከሮሜ ወዘተ የተለያዩ አጣፋጭ የህይወት ቅመሞችን የተመገብነው?

ይህ ጠፊው ሠውነታችን በተገቢው መንገድ ካልያዝነው እንደሚጎዳ ሁሉ መንፈሳችንም እንዲሁ ነው የሚገርመው ለስጋችን የምንመገበው ምግብ ለመንፈሳችን ምንም አይጠቅምም ለመንፈሳችን የምንመገበው ቃለ ግን ለስጋ ይጠቅማል ለዚህም ነው በምሣሌ 4፡20 ልጄ ሆይ ንግግሬን አድምጥ ወደ ቃሌም ጆሮህን አዘንብል ከአይንህም አታርቃት በልብህም ውስጥ ጠብቃት ለሚያገኙዋት ህይወት ለስጋቸውም ሁሉ ፈውስ ነውና ያለው።

ማር ጣፋጭ ነው ሃይልም ለስጋ ይሰጣል ብለን እንወስደዋለን ግን ብዙ ከበላነው ያቅለሸልሻል ታዲያ ብዙ ብንበላው የማይሰለች ከማር ከወለላ ይልቅ የሚጣፍጠውን የእግዚአብሔር ቃል ከዳዊት 119፡103 ቃል ለጉሮሮዬ ጣፋጭ ነው ከማርና ከወለላ ይልቅ ለአፌ ጣፈጠ የሚለውን ሳናቋርጥ ብንወስድ የበለጠ ይጣፍጣል እንጂ አያቅለሸልሸንም፤ ለሠውነታችን የተለያየ ምግብ አብዝተን ብንበላ ውጤቱ ቁንጣን ውፍረት፤ በሽታ፤ ጭንቀት ድካም ወዘተ. ነው ለመንፈሳችን ከእግዚአብሔር ቃል አብዝተን ብንበላ ግን ውጤቱ ጥንካሬ፤ ፈውስ፤ ደስታ፤ ሠላም፤ ሕይወት ለመንፈሳችን ለስጋችንም ይሆናል። ኤርሚያስ ይሄ ገብቶት በም 15፡16 ላይ ቃልህ ተገኝቷል እኔም በልቼዋለሁ አቤቱ የሠራዊት አምላክ ሆይ በስምህ ተጠርቻለሁና ቃልህ ሃሴትና የልብ ደስታ ሆነኝ አለ።

እስኪ ራሳችንን እንጠይቅ በሥራ፤ በትምህርት ቤት በኑሮ ከሚገጥሙን ሰዎች ጋር ያለን ግንኙነት እንዴት ነው? እኛ በተሰጠን ሃላፊነት ለእግዚአብሔርና ኃላፊነቱን ለሰጠን ታምነን በመገኘታችን ያ ታማኝነታች ለአንዳንድ ሰዎች እንደ ልብ መሆን ስላልተመቻቸው በእኛ ላይ ህብረት አድርገው ያላደረግነው ያልሆነውን ሆነ ብለው ቢወነጅሉን የእኛ መልስ ምን ይሆን መቆጣት፤ መበሳጨት ቂም መያዝ፤ ምነው ባላደረግኩት ማለት

*ነው ወይስ የእግዚአብሔርን ቃል የምግብ ማውጫ ሜኑ ገለጥ አድርገን ከ1ኛ ጴጥ 3፡16 በክርስቶስ ያለውን መልካሙን ኑሮአችሁን የሚሳደቡ ሰዎች ክፉ እንደምታደርጉ በሚያምኑበት ነገር እንዲያፍሩ በጎ ህሊና ይኑራችሁ የሚለውን መንፈስን አጠንክሮ ቱግ ያለውን ሥጋ የሚያተነፍሰውን ጣፋጭ ምግብ አዘን ተመግበን ተከታዩን ዲዘርት ደግሞ ከዚያው ሜኑ ከ1ጴጥ 2፡12 እግዚአብሔርን ያከብሩ ዘንድ በአህዛብ መካከለ ኑሮአችሁ መልካም ይሁን የሚለውን ጣፋጭ ኬክ ተመግበን እግዚአብሔርን እናስከብር ይሆን?*

*የጾታችን ተቃራኒ የሆኑ ሰዎች በወንድነታችን ወይም በሴትነታች ሊያጠምዱን ቢመጡ ባማሩና በሚገርሙ ቃላቶች ፍቅራቸውን ቢገልጹ፤ እንዲህና እንዲያ ሆንኩላችሁ ቢሉ፤ አምረውና ተውበው በመልካም መዓዛ ታጅበው ቢመጡ እንቢ ብለን ስንቀር ተከትለው እየመጡ ምን ላድርግ ፍቅር ነው እያሉ ቢጎተጉቱን ቢያባብሉን መልሳችን በመሣፍንት 16፡1 ጀምሮ እንዳለው እንደ ሣምሶን በደሊላ ፍቅር እንደተነደፈ ተነድፈን አይናችንን ጨፍነን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆነውን ሰውነታችንን አሳድፈን ስጋችንን እንጥላለን ወይም ከ2ጢሞ 2፡22 ከክፉ የጉልማሳነት ምኞት ሽሽ፤ በዘፍ 39፡7-12 እንዳለው ዮሴፍ እምቢ ብሎ ልብሱን በጶጢፋራ ሚስት እጅ ላይ ትቶላት ሸሸ የሚለውን ኃይል ሰጪ ምግብ ከእግዚአብሔር የቃል መዓድ እንመገብ ይሆን?*

*ደህንነታች ለማስጣል ቅድስናችን እንዲረክስ ጠላት በተለያየ ዘዴ ለዓይን የሚስብና የሚማርክ ቅመሱኝ፤ ብሉኝ፤ እዩኝ፤ ዳሱኝ የሚያስብል የሓጥያት ግብዣ ሲያቀርብልን በዘዴው ተታለን በወጥመዱ እንያዛለን? ወይንስ አንተ ጠላት ነህ የመጀመሪያውን አዳም ያታለልከው በቃሉም ስለአንተ እንዲህ ይላል ከዮሐ 10፡10 ክፉው ሊገድል ሊያጠፋ ሊያርድ እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤ ከኤፌ 4፡27 ለዲያብሎስ እድል ፈንታ አትስጡት ከያዕ 4፡7 ለእግዚአብሔር ተገዙ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙት ከእናንተ ይሸሻል የሚሉትን የተለያየ ንጥረ ነገር የያዙ ትኩስና ጠላትን የሚያቃጥሉ ለእኛ ግን ጉልበት የሚሆኑ ጠንካራ ምግቦችን አባታችን ከሰጠን መዓድ እንበላስ ይሆን?*

*ለሰውነታችን ቅርጽ ማጣት አልፈው ተርፈው በሽታን የሚያመጡትን የምግብ ዓይነቶች ምንም አጣፍጠው ቢያቀርቡልን በፍጹም ለኔ ስለማይስማሙ አልበላም ብለን እንደምንጠየፋቸው ሁሉ መንፈሳችንን የሚጎዱና የሚያቆሽሹ እንደ ዝሙትና፤ መዳራትና ጣኦትን ማምለክ፤ ምዋርትና ጥል፤ ክርክርና ቅንአት፤ ቁጣና አድመኝነት፤ መለያየትና መናፍቅነት፤ ምቀኝነትና መግደል፤ ሥካርና ዘፋኝነት፤ ሰውን ከሰው ጋር ማጋጨትና ውሸት የተባሉትና ሌሎችም መንፈሳችንን በክፉ መርዛማነታቸው መርዘው የሚያንሳቁሉ ወደ ስጋችንም ተዛምተው ለጉዳት የሚዳርጉ በአቅራቢያችን ያሉ መንፈሳዊ ሰዎች እምነት ላይ ጥቁር ነጥብ የሚያስጥሉና እግዚአብሔርን የማያስከብሩ የተበከሉ ምግቦች ጥፋታቸውን አውቀን እንኳን ልበላ ባሉበት ለማለፍ እንኳን አለርጂክ ነኝ መቼ ይሆን የምንል ?*

*ወገኖቼ ለሥጋችን ጎጂ የሆኑትን አንበላም እያልን ለመንፈሳችን ግን ያገኘነውን ሳናማርጥ እየበላን እኮ ነው ገና አንድ ሲናገሩን ያዙኝ ልቀቁኝ የምንል ለምን ብለው ሲጠይቁን አንተ/ ቺ ማን ሆነህ ነው የምትጠይቀኝ ጥፋታችንን ሲነግሩንማ ፀጉራችን በንዴት ይቆምና በቁጣ ስንት መዓት ከአንደበታችን እናወጣለን። ደግሞ ይባስ ብለን በዚሁ ክፉ በተናገርነበት አንደበታችን ምርቃትን እናወጣለን ተቃራኒ ነገር እርግማንና ምርቃት ሁለት አብረው የማይሄዱ እሳትና ጭድ ናቸውና ምርቃትን ልብ ያለው ይምረጥ።*

*የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ልብ በሉ ማርና ቅቤ፤ ፍራፍሬና አትክል፤ ዓሣና ሥጋ በአጠቃላይ ለሰው ልጆች ጤናማ ናቸው የምትሏቸውን ምግቦች ዘርዝሩአቸው እስክትጠግቡ ትበሏቸው ይሆናል ከዚህ በኋላ ግን ይመራሉ ለማየት እንኳን ያስጠላሉ ግን አብዝተው በተመገቡት ቁጥር የማይጠገብ ጣእሙም እየጨመረ እየጨመረ የሚሄድ ምግብ ግን ከእግዚአብሔር መዓድ ላይ ጊዜ ወስደን አጣጥመን እያንዳንዱን ቃልና ዓርፍተ ነገር አላምጠን አልመን የምንውጠው የቃል ምግብ ነው። ለነፍስም ለሥጋ የሚሆን እና ወገኖቼ የነፍስም የሥጋም ምግብ እንዲሆንልን ሕዝ 3፡3 እንደተጻፈው መንፈሳዊ አፋችንን ከፍተን ቃሉን እንጉረስ እንብላው እግዚአብሔር በሰጠንም በዚህ ቃል ሆዳችንን እንሙላ በአፋችንን እንደ ማር ለዘለአለም ይጣፍጣል።*

*እንዲሁ ይሁንልን!!*

*በሃብታሙ አስረስ (ሃብቴ)*

## ***ያልተለወጠው የድመቷ ባህሪ***

*በአንድ ወቅት አንድ ሰው ምግብ ሲበላ ድመቱን ሻማ ይዛ መቆም አሰለጠናት አሳዳጊዋ በቂ የሆነ እንክብካቤ በየቀኑ ያደርግላታል በፊት አደና ትመገብ የነበረች ሲሆን አሁን ግን ተዘጋጅቶላት ትበላለች እናም በዚሁ መልኩ ለብዙ ዓመት ቤተሰቡ እራት ሲበሉ ድመቷ ሻማ እያበራች ትቆማለት አንድ ቀን ግን እንዲህ ሆነ የድመቷ ባለቤት ሊፈትናት ፈልጎ ቤተሰቡ እራት እየበላ እሷም ሻማውን እያበራች ቆማ ፊትለፊት የሞተ አይጥ ጣለ ድመቷም አይጧን የጎሪጥ አይታ ዝም አለች ይህ ስላስደሰተው ቀጠለና በሕይወት ያለች ሌላ አይጥ ፊት ለፊቷ ለቀቀ ያኔ ነበር የድመቷ ያልተለወጠ ማንነቷ የተገለጠው፤ ሻማውን ወደ መሬት ወርውራ አይጧን ለመያዝ እሮጠች በዚህም ምክንያት ቤቱ በጨለማ ተዋጠ ድመቷ በብዙ እንክብካቤና በቂ ምግብ እየቀረበላት ትኖር የነበረች ብትሆንም ነገር ግን ካለመለወጧ የተነሳ ለብዙ ዓመት የተወቸውን አይጥ ማሳደድ ጀመረች ብዙዎቻችን ካለመለወጥ የተነሣ ድሮ የተውናቸው ባሕሪዎቻችን ብቅ እያሉ ልናበራ የተጠራንለት የወንጌል ብርሃን በኛ ምክንያት በዙሪያችን ባሉ ሰዎች ላይ ጨልሞ ይገኛልና እግዚአብሔር ሁላችንን አንድንነቃ ይርዳን።*

***ይህ ጽሁፍ ወንድም እንግዳየሁ ጥላሁን ካነበብኩት ብለው የላኩልን ነው***

## የትምህርት ዓምድ

## የእውነተኛ ክርስቲያን ባህሪ

ካለፈው የቀጠለ.. መጋቢ ምህረቱ ለጄቦ የእውነተኛ ክርስቲያን ባሕሪ በሚል ርእስ የጀመሩትን ተከታታይ ትምህርት ቀጣዩን ክፍል ይዘንላችሁ ቀርበናል መልካም ግዜ በእውነተኛ የክርስቲያናዊ ባህሪ በመመላለስ እንድንኖር የተጠራንበት ሕይወት ነው።

በኤፌ 2፡10 እኛ ፍጥረቱ ነንና እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን። ክርስቲያናዊ ባሕሪ ኖሮን እንደሚገባ መመላለሳችን የመዳናችን ምልክት ነው፤ ምክንያቱም በክርስቶስ ያገኘነው ሕይወት የሚገለጥ ሕይወት ነው። በ1ኛ ዮሐ 3፡9 ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢያትን አያደርግም ዘሩ በእርሱ ይኖራልና ከእግዚአብሔር ተወልዷልና ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም የእግዚአሔር ልጆችና የዲያቢሎስ ልጆች በዚህ የተገለጡ ናቸው። እንግዲህ የእግዚአብሔር ቃል የሚያመለክተው በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን ዳግመኛ መወለድ የእግዚአብሔር ልጆች የሆንን የእግዚአብሔር ህዝብ መለያው ቃሉን በማመን መታዘዝ ነው። የምናፈራው ፍሬ ማንነታችንን የሚገልጥ ከሆነ ቆም ብለን በህይወቴ የማፈራው ምን ዓይነት ፍሬ ነው ብለን ልናስብ ይገባናል ማለት ነው።

እግዚአብሔርን የማወቃችን እርሱን የመውደዳችንም መለኪያ ነውና፤ በ1ኛ ዮሐ 2፡3 ትእዛዙን ብንጠብቅ በዚህ እንዳወቅነው እናውቃለን በብሉይ ኪዳን የእሥራኤል ሕዝብ ከሌላው አህዛብ የተለዩ እንዲሆኑለት እግዚአብሔር ህግን ሰጣቸው በብሉይ ከ600 የሚበልጡ ህጎች አሉ፤ ይህ ህግ ከጎረቤቶቻቸው ሃገሮች በአመጋገባቸው በአለባበሳቸው በእርሻ ሥራቸው ፈጽመው የተለዩ ያደረጋቸው ነበር፤ በኢሣ 52፡11 እናንተ የእግዚአብሔር እቃ የምትሸከሙ ሆይ እልፍ በሉ እልፍ በሉ ከዚያ ውጡ ርኩስን ነገር አትንኩ፤ የእሥራኤል ህዝብ የእግዚአብሔር ህዝብ ናቸው የሚያስኛቸው እግዚአብሔር የሰጣቸው ህግ በእነርሱ ላይ መታየቱ ነው፤ በመንፈስ ቅዱስ መረዳት ቃሉን በተሞላን መጠን በሕይወታችን የሚገለጠው እውነተኛ ክርስቲያናዊ ባህሪ ነው። የእግዚአብሔርም ቃል የሚለን ቃሉ በሙላት ይኑርባችሁ ይላል፤ ቆላ 3፡15 በቃሉ ተሞልተን በህይወታችን የክርስቶስ ህይወት ተገልጦ እንዲታይ ቃሉን የምናጠናበት ይህን ቅደም ተከተል ብንከተል እንጠቀማለን።

1ኛ- የቃሉን ሥልጣንና ኃይል ማወቅና ማመን ይህ ማለት የእግዚአብሔር ቃል እግዚአብሔር እፍ ያለበት የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት ህያውና በሰው ሕይወት አልፎ የሚሰራ እንደሆነ ማመናችን ለቃሉ ከፍተኛ ክብርና ግምት እንድንሰጥ ያደርገናል ከዚህ በኋላ ነው ለቃሉ ጊዜ ሰጥተን እንኳን ቃሉን ማጥናት የምንችለው። ዕብ 4፡12 የእግዚአብሔር ቃል ህያው ነውና የሚሰራም ሁለት አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅ የተሳለ ነው።

2ኛ- የምናጠናውን ክፍል መምረጥ ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ያሉትን እያንዳንዳቸው መጽሐፍት በመንፈስ ቅዱስ የተደረሱ ናቸው ጊዜ አግኝተን ሁሉንም ብናጠና መልካም ነው፤ ነገር ግን ቅድሚያ ሰጥተናቸው ልናጠናቸው የሚገቡን ክፍሎች አሉ። ለምሣሌ መልእክቶች በሙሉ ከሮሜ መልእክት ጀምሮ ቅድሚያ ሰጥተን ልናጠናቸው ይገባል። ምክንያቱም በክርስቶስ ያገኘነውን አዲስ ሕይወት እንድናገኝ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ስለእኛ የከፈለውን ዋጋና አርሱን በማመንና በማወቅ ያገኘነውን በረከቶች እንድንረዳና ይህን ክቡር ሰማያዊ ጥሪ የተቀበልን ቅዱሳን በየእለቱ የክርስትና ጉዞ በዚህ ዓለም ስንኖር በያለንበት ቦታ በተጠራንበት በመጠራታችን እንዴት መመላለስ አንደሚገባን ከሮሜ መልእክት ጀምሮ ያሉ ክፍሎች በስፋትና በጥልቀት ያብራሩልናል፤ ቀጥሎ ወንጌላትን ማለት ከማቴዎስ እስከ ዮሐንስ በጥናት መልክ ብናጠናቸው መንፈስ ቅዱስ ቃሉን ለመንፈሳችን በመግለጥ ለውስጥ ሰውነታችን ውበትን፤ ጥንካሬን፤ ጤንነትንና ብስለትን ይሰጠናል። ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ ደግሞ ብንከተል ብዙ እንጠቀማለን። ይቀጥላል…

በመጋቢ ምሕረቱ ለጄቦ




የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን በቦስተን
ETHIOPIAN EVANGELICAL CHURCH BOSTON
88 TREMONT STREET, BOSTON, MA, 02108
T: 617-523-5058 F: 617-523-5058
www.eecBoston.org